7) Gaaffii pirojektii investimentii Waldaalee Hojii Gamtaafi Intarpiraayizii Maayikiroofi Xixiqqaa Ce'aniin dhiyaatu kan simatamu sadarkaa Godinaa yookiin magaalaa Naannoof ittiwaamamanitti ta'a.
8) Gaaffiin simannaa pirojejektii lafa investimentii babal'ifannaa dhiyaatu kamiyyuu Biirichatti dhiyaachuun kan murtaa'u ta'a.
9) Gaaffiin pirojektoota investimentii sadarkaa Biirootti dhiyaatu kamiyyuu dursa Hoogganaa Biirichaatiin yookiin nama inni bakka buuseen yookiin Itti Aanaa Hoogganaa Biirichaafi Damee dhimmi ilaallatuun gara qaama simatutti qajeelfamuu qaba.
10) Gaaffiin pirojektii investimentii lafa dursee qophaa'e irratti simatame karaa Biirichaatiin Boordiif kan dhiyaatu ta'a.

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የተስተናገደ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ጥያቄ በቢሮው በሚጠየቅበት ጊዜ፣ የመሬት ቢሮ መሬቱን በአድራሻው፣ በፕሮጀክት ዓይነትና በመሬቱ ልዩ መገኛ ቦታ (ኤክስ-ዋይ ኮኦርዲኔት) በመለየት ማቅረብ አለበት፡፡
5) በመካከለኛና በአዳጊ ከተማ ውስጥ የሚካሄድ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ጥያቄ የሚስተናገደው በከተማው ደረጃ ባለው የቢሮው መዋቅር ይሆናል፡፡
6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 - 4 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሃብት በማፍራት ወደ ኢንቨስትመንት ስራ በተሸጋገሩ አርሶ አደሮች፣ በአርብቶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች የሚቀርብ የኢንቨስትመንት ጥያቄ የሚስተናገደው በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደሩ የኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡
7) በሕብረት ስራ ማሕበራትና በተሸጋገሩ ማይክሮና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የሚቀርብ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ጥያቄ የሚስተናገደው በዞን ወይም ለክልል ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ደረጃ ይሆናል፡፡
8) ማንኛውም የኢንቨስትመንት መሬት ማስፋፊያ የሚቀርብ ጥያቄ መስተንግዶ ለቢሮው ቀርቦ የሚወሰን ይሆናል፡፡
9) ለቢሮ ደረጃ የሚቀርብ ማንኛውም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ጥያቄ በመጀመሪያ በቢሮው ሃላፊ ወይም እሱ በወከለው ሰው ወይም በምክትል ቢሮ ሃላፊውና ጉዳዩ በሚመለከተው ክፍል በኩል ለመስተንግዶው አካል መመራት አለበት፡፡
10) አስቀድሞ በተዘጋጀ መሬት ላይ የተስተናገደ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ጥያቄ በቢሮው በኩል ለቦርድ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

4) Where the request of investment project accepted as per Sub Article 3 of this Article is presented to it by the Bureau, the Land Bureau shall present such land by identifying it in its address, type of project and distinct location/situation of the land (XY Coordinate).
5) Applications of investment projects to be undertaken in the Medium and Developing City shall be accepted by the structure of the Bureau found at the City level.
6) Without prejudice to provisions under Sub Articles 1 - 4 of this Article, investment applications submitted by the farmers, pastoralists, or semi pastoralists who have acquired assets and moved up to investment activities shall be received through the Woreda Investment and Industry Office or through City Administration.
7) Applications of investment projects submitted by Cooperative Associations and promoted Micro and Small Enterprises shall be received at the Zonal level or at the Cities which are accountable to the Region.
8) Reception of any application of the project submitted for expansion of investment land shall be submitted to the Bureau for decision.
9) Any applications of investment projects submitted at the Bureau level shall first be referred to the receiving body by the Head of the Bureau or person represented by him or Deputy Head of the Bureau and by the concerned branch.
10) Application of investment projects received on the already prepared land shall be submitted to the Board through the Bureau.

## 9. Ulaagaalee Gaaffii Pirojektii Investimentii

1) Namni hojii investimentii irratti bobba'uuf pirojektii investimentii dhiyeessu ulaagaalee armaan gadii guutuu qaba:

(a) Karoora bu'a qabeessummaa pirojektii investimentii qoratamee dhiyaate;

(b) Kaappitaalli ka'umsa pirojektichaa yoo xiqqaate qarshii 20,000,000.00 (Miliyoona Digdama) ta'uu;

(c) Ragaa sochii maallaqa baankii yoo xiqqaate kan ji'a 6 (jahaa) agarsisuufi kaappitaala hojiif barbaachisu keessaa yeroo gaafficha dhiyeessutti akkaataa gosa pirojektiitiin hanga kaappitaalichaa keessaa % 30 (soddoma) qusachuu yookiin bittaan maashinootaafi meeshaalee hojii karoorfateen walqunnamtii qabu raawwatamee ragaa yookiin nagahee % 30 (soddoma) madaalu agarsisu dhiyeessuu;

(d) Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 1 (c) jalatti kan tumame jiraatus, Paarkii Industirii keessatti industiriiwwan bu'aalee oomisha qonnaa yoo ta'e, %15 (kudha shan) qusachuu isaa agarsiisu yookiin bittaan maashinootaafi meeshaalee hojii karoorfateen walqunnamtii qabu raawwatamee yoo jiraate ragaa yookiin nagahee dandeettii % 15 (kudha shan) madaalu agarsisu dhiyeessuu;

(e) Pirojektichi dhaabbata daldalaatiin kan gaggeeffamu yoo ta'e, barreeffama hundeeffamaa qaamaa aangoo qabuun galmaa'ee mirkanaa'e, waraqaa eenyummaa yookiin paaspoortii hojii gaggeessaa haaromfame suura waliin dhiyeessuu;

(f) Pirojektii investera biyya alaa yookiin Investera biyya keessaafi alaa waliin qindaa'aniin gaggeeffamu yoo ta'e, Komishinii Investimentii Itoophiyaa irraa hayyama investimentii kennameefi kooppii galmee isaa achitti baname;

## 9. የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ጥያቄ መስፈርቶች

1) በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ ለመሰማራት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት የሚያቀርብ ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፦

(ሀ) ተጠንቶ የቀረበ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ውጤታማነት ዕቅድ፤

(ለ) የፕሮጀክቱ መነሻ ካፒታል ቢያንስ ብር 20,000,000.00 (ሃያ ሚሊዮን) መሆን አለበት፤

(ሐ) ቢያንስ የ6 (ስድስት) ወር የባንክ ሂሳብ (ገንዘብ) እንቅስቃሴን የሚያሳይ ማስረጃ እና ለስራው ከሚያስፈልገው ካፒታል ውስጥ ጥያቄውን በሚያቀርብበት ጊዜ እንደ ፕሮጀክቱ ዓይነት ከካፒታሉ መጠን ውስጥ 30% (ሰላሣ ከመቶ) መቆጠቡን ወይም የማሽኖችና ካቀደው ስራ ጋር የሚያያዙ መሣሪያዎች ግዢ መፈጸሙን የሚያሳይ ማስረጃ ወይም ደረሰኝ 30% (ሰላሣ ከመቶ) የሚመጥን ማቅረብ፤

(መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) ስር የተደነገገው ቢኖርም፣ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚሰሩ የግብርና ምርት ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ከሆነ 15% (አስራ አምስት ከመቶ) መቆጠቡን የሚያሳይ ወይም የማሽኖችና ካቀደው ስራ ጋር የሚያያዙ መሣሪያዎች ግዢ ተፈጽሞ ከሆነ ማስረጃ ወይም ደረሰኝ 15% (አስራ አምስት ከመቶ) የሚመጥን ማቅረብ፤

(ሠ) ፕሮጀክቱ በንግድ ድርጅት የሚካሄድ ከሆነ፣ ሥልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ የተረጋገጠ የመመስረቻ ጽሁፍ፣ የታደሰ የስራ አስኪያጁ የመታወቂያ ወረቀት ወይም ፓስፖርት ከፎቶግራፍ ጋር ማቅረብ፤

(ረ) ፕሮጀክቱ በውጭ ሃገር ባለሃብት ወይም የሃገር ውስጥ ኢንቨስተርና ከውጭ ሃገር ኢንቨስተሮች ጋር በቅንጅት የሚካሄድ ከሆነ፣ ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተሰጠውን የኢንቨስትመንት ፈቃድ እዚያው የተከፈተው መዝገብ ኮፒ ማቅረብ፤

## 9. Requirements For Requesting Investment Projects

1) Any person submitting application of investment project to engage on investment works shall meet the following requirements:

(a) Feasibility plan of investment project submitted after being researched;

(b) The startup capital of the project shall be minimum Birr 20,000,000.00 (twenty million),

(c) Submit evidence indicating the bank account transaction for at least 6 (six) months and saving of 30% (thirty) of the total capital required for the work at the time of submitting the application depending on the type of project or producing evidence or receipt indicating the performed purchase of machinery and equipment related to the planned work which is equivalent to its 30 % (thirty);

(d) Notwithstanding to Sub Article 1(c) of this Article, submit evidence or receipt of capacity of 15% (fifteen) in the case of agricultural products of the Industrial Park project or evidence or receipt procurement of machinery and equipment related to the planned work providing a demonstration of ability equivalent to 15% (fifteen).

(e) Where the project is conducted by commercial organization, submit memorandum of establishment registered and approved by the competent Authority, renewed identity card or passport of the manager along with photograph;

(f) Where the project is carried out by a foreign investor or by the coordination of domestic and foreign investors, submit investment license issued for him by the Ethiopian Investment Commission and a copy of its registration opened there;

(g) Investera dhuunfaa yoo ta'e, kooppii waraqaa eenyummaa yookiin paaspoortii haaromfame suura waliin;

(h) Waldaa Hojii Gamtaa yoo ta'e, bu'uura seera rogummaa qabuutiin hundaa'uu isaa ragaa ibsu qaama aangoo qabu irraa kenname, waraqaa eenyummaa yookiin paaspoortii hojii gaggeessaa haaromfame suura waliin; fi

(i) Unka gaaffii pirojektii investimentiif qophaa'e irratti ragaa qabatamaafi dhugaa ta'e guutuudhaan mallattoo isaatiin kan mirkanaa'e dhiyeeffachuu qaba.

2) Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 1 (b-d) jalatti kan tumame jiraatus, namni kalaqa addaa beekamtiin kennameef qabaatee yaada isaa gara hojii investimentiitti jijjiiruuf pirojektii investimentii dhiyeeffate kaappitaala ka'umsaafi sochii maallaqa baankii akka dhiyeeffatu hin dirqamu.

**10. Calallii Duraa Pirojektii Investimentii**

Calalliin duraa pirojektii investimentii sadarkaa pirojektichi itti simatametti kan raawwatamu ta'ee, bu'aan isaa investera gaaffii pirojektii dhiyeesseef guyyaa hojii walitti aanan 2 (lama) keessatti beeksifamuu qaba.

**11. Xiinxala Pirojektii Investimentii**

1) Pirojektiin investimentii simatame kamiyyuu xiinxalaaf kan dhiyaatu ulaagaalee gaaffii pirojektii investimentii yoo guute qofa ta'a.

2) Pirojektiin investimentii ulaagaalee xiinxalaa armaan gadiitiin kan madaalamu ta'a:

(a) Bu'a qabeessummaan sochii faayinaansii isaa kan mirkanaa'e ta'uu;

(b) Sadarkaa ittifayyadama teknolojii ammayyaa pirojektichaa;

(c) Pirojektichi sharafa biyya alaa kan argamsiisu yookiin qusatu ta'uu;

(d) Kaappitaalli hojichaaf karoorfame gahaa ta'uufi irra caalatti madda maallaqaa mataa ofii kan qabu ta'uu;



(ሰ) የግል ኢንቨስተር ከሆነ፣ የታደሰ የመታወቂያው ወይም ፓስፖርት ኮፒ ከፎቶግራፍ ጋር ማቅረብ፤

(ሸ) የሕብረት ሥራ ማህበር ከሆነ፣ አግባብነት ባለው ህግ መሠረት መመስረቱን የሚያሳይ ማስረጃ ሥልጣን ካለው አካል የተሰጠ፣ የታደሰ የስራ አስኪያጁ የመታወቂያ ወረቀት ወይም ፓስፖርት ከፎቶግራፍ ጋር፤ እና

(ቀ) በተዘጋጀው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ጥያቄ ቅጽ ላይ ተጨባጭና እውነተኛ ማስረጃ በመሙላት በፊርማው ተረጋግጦ ማቅረብ አለበት።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ - መ) ሥር የተደነገገው ቢኖርም፣ እውቅና የተሰጠው ልዩ ፈጠራ ኖሮት ሃሣቡን ወደ ኢንቨስትመንት ስራ ለመለወጥ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ያቀረበ ሰው የመነሻ ካፒታልና የባንክ ሂሣብ እንቅስቃሴ ማስረጃ እንዲያቀርብ አይገደድም።

**10. የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ቅድመ ማጣሪያ**

የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ቅድመ ማጣሪያ ፕሮጀክቱ በተስተናገደበት ደረጃ የሚፈጸም ሆኖ፣ ውጤቱንም በ2 (ሁለት) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የፕሮጀክቱን ጥያቄ ላቀረበው ኢንቨስተር እንዲያውቀው መደረግ አለበት።

**11. የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ግምገማ**

1) ማንኛውም የተስተናገደ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ለምርመራ የሚቀርበው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ጥያቄ መስፈርትን ካሟላ ብቻ ይሆናል።

2) የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት በሚከተሉት የምርመራ መስፈርቶች የሚመዘን ይሆናል:-

(ሀ) የፋይናንስ እንቅስቃሴው ውጤታማነት የተረጋገጠ መሆኑ፤

(ለ) የፕሮጀክቱ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ደረጃ፤

(ሐ) ፕሮጀክቱ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኝ ወይም የሚቆጥብ መሆኑ፤

(መ) ለሥራው የታቀደው ካፒታል በቂ መሆኑና በአመዛኙ የራሱ የሆነ የገንዘብ ምንጭ ያለው መሆኑ፤



(g) In case of private investor, copy of renewed identity card or passport along with photographs;

(h) Where the project is conducted by Cooperative Association, submit evidence describing that it is established in accordance with the pertinent law provided by the authorized body, renewed identity card or passport of the manager along with photograph; and

(i) Fill factual and genuine evidences on the form prepared for investment project application ascertained by his signature and shall submit same.

2) Notwithstanding to provision under Sub Article 1 (b – d) of this Article, a person who has a unique invention that has got recognition submitted an investment project with a view to convert his idea into an investment work shall not be required to submit initial capital and bank account transaction.

**10. Preliminary Screening of Investment Project**

The preliminary screening of investment project shall be performed at the reception stage of the project; and the results shall be notified to the investor who submitted the project request within 2 (two) consecutive working days.

**11. Investment Project Analysis**

1) Any received investment project shall be submitted for analysis only if fulfills the criteria of application for investment projects.

2) The investment project shall be evaluated by the following criteria of analysis:

(a) That the profitability of its financial operations is proven;

(b) Degree of the project to apply modern technology;

(c) That the project generates or saves foreign currency;

(d) That the capital planned for the work is sufficient and it is mainly obtained from its own source of funding;

(e) Hawaasa naannootiif carraa hojii ittifufiinsa qabu kan uumu ta'uu;
(f) Pirojektiin dhiyaate naannoofi hawaasa irratti dhiibbaa hin malle kan hin geessifne ta'uu;
(g) Pirojektichi walitti hidhamiinsa gabaa qabaachuu;
(h) Akka barbaachisummaa isaatti, pirojektoota investimentii kanneen biroo waliin walitti hidhamiinsa duraafi boodaa kan qabu ta'uu isaa;
(i) Pirojektichi aadaa, duudhaafi safuu hawaasa naannoo waliin kan wal hin faalleessine ta'uu;
(j) Facaatii pirojektoota investimentii Naannichaa akka walgitu taasisuu keessatti gahee qabaachuu;
(k) Pirojektichi mootummaadhaan dursa kan kennameef ta'uu; yookiin
(l) Pirojektichi dirqama hawaasummaafi sadarkaalee eegumsa naannoo kan bahu ta'uu.

3) Ulaagaan xiinxalaa Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 2 (a fi d) jalatti tumame akkuma barbaachisummaa isaatti nama kalaqa addaa qabaatee pirojektii investimentii dhiyeeffatu irratti raawwatiinsa kan hin qabaanne ta'a.

4) Ulaagaaleen xiinxala pirojektii investimentii Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 2 jalatti kan tumame akkuma eegamanitti ta'ee, pirojektiin investimentii dorgommiin yookiin dorgommiin ala lafti investimentii murtaa'uufii kan danda'u qabxii madaallii xiinxala waliigalaa keessaa % 50 (shantama) fi isaa ol yoo argateedha.

5) Qabxiileen madaallii Keewwata kana jalatti tarreeffaman Qotee Bulaa, Horsiisee Bulaafi Gamisa Horsiisee Bulaa irratti raawwatiinsa hin qabaatan.

(ሠ) ለክልሉ (ለአካባቢው) ሕብረተሰብ ዘላቂነት ያለው የሥራ ዕድል የሚፈጥር መሆኑ፤
(ረ) የቀረበው ፕሮጀክት በአካባቢና በማሕበረሰቡ ላይ አሳስፈላጊ ተጽዕኖ የማያደርስ መሆኑ፤
(ሰ) ፕሮጀክቱ የገበያ ትስስር ያለው መሆኑ፤
(ሸ) እንደ አስፈላጊነቱ ከሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ጋር የቅድመ እና ድህረ ትስስሮች ያለው መሆኑ፤
(ቀ) ፕሮጀክቱ ከአካባቢው ማሕበረሰብ ባሕል፣ እሴትና ልማድ ጋር የማይቃረን መሆኑ፤
(በ) ፕሮጀክቱ የክልሉን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ስርጭት ተመጣጣኝ እንዲሆን ለማድረግ አስተዋጽዖ የሚያደርግ መሆኑ፤
(ተ) ፕሮጀክቱ በመንግሥት ቅድሚያ የተሰጠው ፕሮጀክት መሆኑ፤ ወይም
(ቸ) ፕሮጀክቱ ማሕበራዊ ሃላፊነቱንና የአካባቢ ጥበቃ ደረጃዎችን የሚወጣ መሆኑ።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ እና መ) ሥር የተደነገጉት የምርመራ መስፈርቶች እንደ አስፈላጊነቱ ልዩ ፈጠራ ኖሮት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ባቀረበ ሰው ላይ ተፈጻሚነት የማይኖረው ይሆናል።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገጉት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ምርመራ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ አንድ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት በውድድር ወይም ያለ ውድድር የኢንቨስትመንት መሬት ሊወሰንለት የሚችለው ከአጠቃላዩ የምርመራ መመዘኛ ነጥብ 50% (ሃምሣ ከመቶ) እና ከዚያ በላይ ካገኘ ነው።

5) በዚህ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩት የመመዘኛ ነጥቦች በአርሶ አደር፣ በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

(e) That it creates sustainable job opportunities for the local community;
(f) That the submitted project shall not cause undue impact on the environment and the community;
(g) That the project has got market linkages;
(h) That it has pre and post relationships with other investment projects as necessary,
(i) That the project is not contradictory to the culture, values and customs of the local community;
(j) That it has roles for the fair or equal distribution of investment projects in the Region;
(k) That the project is the one which is given priority by the Government;
(l) The project discharges its social responsibility and standards of environmental protection.

3) The analysis criteria provided under sub article 2 (a and d) of this Article may not be applicable to the person who submits an investment project having unique invention as may be necessary.

4) Without prejudice to Sub Article 2 this Article, an investment project may be provided investment land through competition or without competition if he scores 50% (fifty percent) and above of the total analysis evaluation criteria or points.

5) The evaluation points listed under this Article shall not be applicable to the farmer, pastoralist and semi-pastoralist.

### 12. Adeemsa Xiinxala Pirojektii Investimentii

1) Xiinxalli pirojektii investimentii kan gaggeeffamu sadarkaa Biirichaatti ta'ee, ogeessota rogummaa qabaniin xiinxalamee Biirichaaf kan dhiyaatu ta'a.
2) Xiinxalli pirojektii gaggeeffamu kamiyyuu hojimaata dhimma kanaaf diriire irratti hundaa'uun gaggeeffamuu qaba.
3) Pirojektiin investimentii calalamee dhiyaate guyyoota hojii 5 (shan) keessatti xiinxalli isaa xumuramuu qaba.
4) Xiinxalli pirojektoota karoora pirojektii dorgommiif dhiyaate xiinxaluun kanneen faayidaa ol'aanaa argamsiisuu danda'an adda baasuun sadarkeeffamuu qaba.
5) Bu'aan dorgommii pirojektoota xiinxalamee kanneen sadarkaan 1ffaa hanga 3ffaa ta'an maanajimentii Biirichaatiin mirkanaa'ee qabxii isaan argatan waliin qaama murtii kennuuf dhiyaachuu qaba.

## Kutaa Sadii

## Qonnaan Bulaa, Horsiisee Bulaa yookiin Gamisa Horsiisee Bulaa yookiin Waldaalee Hojii Gamtaa yookiin Intarpiraayizii Maayikiroofi Xixiqqaa Gara Investimantiitti Ce'an

### 13. Haala Qonnaan Bulaan, Horsiisee Bulaan yookiin Gamiisa Horsiisee Bulaan yookiin Waldaaleen Hojii Gamtaa Investimentii Irratti Itti Hirmaatu

1) Qonnaan Bulaan, Horsiisee Bulaan yookiin Gamisa Horsiisee Bulaan qabiyyee lafa isaa yookiin lafa mootummaan pirojektii investimentiif qopheessu irratti dhuunfaadhaan yookiin maatiidhaan yookiin waldaadhaan gurmaa'ee hojii investimentii gaggeessuuf gaaffii pirojektii investimentii caasaa Biirichaa sadarkaa Aanaa yookiin Magaalatti kan dhiyeeffatu ta'a.

### 12. የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ምርመራ ሂደት

1) የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ምርመራ የሚካሄደው በቢሮው ደረጃ ሆኖ፤ አግባብነት ባላቸው ባለሙያዎች ተመርምሮ ለቢሮው የሚቀርብ ይሆናል፡፡
2) ማንኛውም የሚካሄድ የፕሮጀክት ምርመራ ለዚሁ ጉዳይ በተዘረጋው አሰራር ላይ በመመስረት መካሄድ አለበት፡፡
3) ተጣርቶ የቀረበ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት በ5 (አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ምርመራው መጠናቀቅ አለበት፡፡
4) የፕሮጀክቶች ምርመራ ለውድድር የቀረበውን የፕሮጀክት ዕቅድ በመመርመር ከፍተኛ ጥቅም ሊያስገኙ የሚችሉትን በመለየት ደረጃ ሊሰጠው ይገባል፡፡
5) የተመረመሩ ፕሮጀክቶች የውድድር ውጤት ከ1ኛ እስከ 3ኛ ደረጃ የሆኑት በቢሮው ማኔጅመንት ተረጋግጦ ካገኙት ነጥብ ጋር ለውሣኔ ሰጪው አካል መቅረብ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር ወይም የሕብረት ስራ ማሕበራት ወይም ወደ ኢንቨስትመንት የተሸጋገሩ ማይክሮና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች

### 13. አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ ወይም ከፊል አርብቶ አደሩ ወይም የሕብረት ሥራ ማሕበራት በኢንቨስትመንት ስራ ላይ የሚሣተፉበት ሁኔታ

1) አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ ወይም ከፊል አርብቶ አደሩ በራሱ የመሬት ይዞታ ላይ ወይም መንግሥት ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክት በሚያዘጋጀው መሬት ላይ በግል ወይም በቤተሰብ ወይም በማሕበር በመደራጀት የኢንቨስትመንት ስራ ለማካሄድ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ጥያቄውን በወረዳ ወይም በከተማ ደረጃ ላለው የቢሮው መዋቅር የሚያቀርብ ይሆናል፡፡

### 12. Process of Analyzing Investment Projects

1) Analysis of investment project shall be conducted at the Bureau level; and shall be analyzed and submitted to the Bureau by the appropriate professionals or experts.
2) Any analysis of investment project to be conducted shall be only based on the operation procedures established for this purpose.
3) Analysis of the screened investment project shall be completed within 5 (five) working days.
4) In the process of analyzing the projects, by analyzing the plan of the project submitted for competition, those generating higher benefits shall be differentiated and ranked.
5) The competition results of the analyzed projects of those ranked 1st up to 3rd shall be submitted to the body passing final decision along with their results after it has been approved by the management of the Bureau.

## Part Three

## The Farmer, Pastoralist or Semi Pastoralist or Cooperative Societies or Micro and Small Enterprises Promoted To Investment

### 13. The Manner For the Farmer, Pastoralist or Semi Pastoralist or Cooperative Societies Engage In Investment

1) The farmer, pastoralist or semi pastoralist may submit his application for investment project to the structure of the Bureau at the Woreda and City levels to conduct investment work on his land possession or on the investment land prepared by the Government to work privately or being organized with his family or in association.

2) Caasaan Biirichaa gaaffii akkaataa Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 1 tiin dhiyaateef ulaagaa simannaa investimentii Qonnaan Bulaan, Horsiisee Bulaan yookiin Gamisa Horsiisee Bulaatiif tumameen xiinxaluun kanneen ulaagaa guutan kan simatu ta'ee, ulaagaalee barbaachisan kan hin guutamne yoo ta'e hanqinoota jiran sirreeffamanii akka dhiyaatan gorsaafi deeggarsa ni kenna.
3) Akkaataa Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 1 tiin gaaffiin dhiyaate ulaagaa barbaachisu guutee kan dhiyaate yoo ta'e, caasaan Biirichaa walitti qabee guyyaa 15tti (kudha shan)tti yeroo tokko Koree Bulchiinsa Investimentii Aanichaa yookiin Magaalichaatiif ni dhiyeessa. Koreen kunis yaada murtii dhiyaateef guyyaa hojii 15 (kudha shan) keessatti ilaaluun karaa caasaa Biirichaatiin qaama bulchiinsa investimentii ittiwaamamuuf kan dabarsan ta'a.
4) Qaamni bulchiinsa investimentii akkaataa Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 3 tiin karaa caasaa Biirichaatiin sadarkaa Godinaa yaadni murtii dhiyaateef irratti murtii kennuun guyyaa hojii 10 (kudhan) keessatti yaada murtii Biirichaaf erguu qaba.
5) Biirichis yaada murtii akkaataa Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 3 fi 4 tiin isaaf dhiyaate xiinxaluun walitti qabee maanajimentii isaatiin guyyaa 15tti (kudha shanitti) yeroo tokko murteessisee walgahii idilee Boordichaa itti aanuuf erguu qaba.
6) Boordichis yaada murtii akkaataa Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 5 tiin dhiyaateef ilaalee yeroo ji'a 1 (tokko) hin caalle keessatti murteessuun qonnaan bulicha, horsiisee bulicha yookiin gamisa horsiisee bulicha beeksisuu qaba.

2) የቢሮው መዋቅርም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የቀረበለትን ጥያቄ ለአርሶ አደሩ፣ ለአርብቶ አደሩ ወይም ከፊል አርብቶ አደሩ በተደነገገው የኢንቨስትመንት መስተንግዶ መስፈርት መሠረት በመመርመር መስፈርቱን ያሟሉትን የሚቀበል ይሆናል፤ አስፈላጊ መስፈርቶችን ያላሟሉ ከሆነ ያሉት ጉድለቶች ተስተካክለው እንዲቀርቡ ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የቀረበው ጥያቄ አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ የቀረበ ከሆነ፣ የቢሮው መዋቅር ሰብስቦ በ15 (አስራ አምስት) ቀን አንድ ጊዜ ለወረዳው ወይም ለከተማው የኢንቨስትመንት አስተዳደር ኮሚቴ ያቀርባል፡፡ ይህ ኮሚቴም የቀረበለትን የውሣኔ ሃሣብ በ15 (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ በመመርመር በቢሮው መዋቅር በኩል ተጠሪ ለሆነለት የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካል የሚያስተላልፍ ይሆናል፡፡
4) የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካሉም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በዞን ደረጃ የቢሮው መዋቅር በኩል በቀረበለት የውሣኔ ሃሣብ ላይ ውሳኔ በመስጠት በ10 (በአስር) የሥራ ቀናት ውስጥ የውሣኔ ሃሣብ ለቢሮው መላክ አለበት፡፡
5) ቢሮውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት የቀረበለትን የውሣኔ ሃሣብ በመመርመር ሰብስቦ በ15 (በአስራ አምስት) ቀን አንድ ጊዜ በራሱ ማኔጅመንት በማስወሰን ለሚቀጥለው የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ መላክ አለበት፡፡
6) ቦርዱም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የቀረበለትን የውሣኔ ሃሣብ መርምሮ ከ1 (ከአንድ) ወር ባልበለተ ጊዜ ውስጥ በመወሰን ለአርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ ወይም ከፊል አርብቶ አደሩ ማሣወቅ አለበት፡፡

2) Structure of the Bureau shall, by analyzing the application submitted to it as per Sub Article 1 of this Article with the reception criteria provided for the farmer, pastoralist or semi pastoralist, receive those who meet the requirements; and where they are unable to meet the necessary criteria, it provides advices and support for the shortcomings to be corrected and submitted back.
3) Where application submitted as per Sub Article 1 of this Article is submitted by satisfying the necessary criteria, structure of the Bureau shall collect it and deliver to the Investment Administration Committee of the Woreda or City once in 15 (fifteen) days. This Committee shall also examine the decision recommendation submitted to it within 15 (fifteen) working days and pass on to the Investment Administration Body to which it is accountable through the Bureau structure.
4) The Investment Administration Body to which the decision recommendation has been submitted as per Sub Article 3 of this Article through the Bureau Structure at the Zonal Level shall render decision on such decision and send its decision recommendation to the Bureau within 10 (ten) working days.
5) The Bureau as well shall analyze the decision recommendation submitted to it as per Sub Article 3 and 4 of this Article and cause to be decided by its management once in 15 (fifteen) days and send it to the next higher Regular Assembly of the Board.
6) The Board shall, by examining the decision recommendation submitted to it as per Sub Article 5 of this Article and deciding it within the time not exceeding 1 (one) month, notify such decision for the farmer, pastoralist or semi pastoralist.

7) Qaamni Bulchiinsaa Investimentii Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 3 -- 5 jalatti ibsaman yeroo jedhame keessatti kan hin murteessine yoo ta'e qonnaan bulaan, horsiisee bulaan yookiin gamisa horsiisee bulaan akkaataa armaan gadiitiin iyyatee murteessifachuu ni danda'a:

(a) Koree Bulchiinsaa Investimentii Aanaafi Magaalaa ittiwaamamni isaa godinaaf ta'e yeroo jedhame keessatti kan hin murteessine yoo ta'e, koree investimentii godinaatti kallattiin iyyatachuun akka dafee murtaa'uuf gochuu ni danda'a. Koreen Godinaas iyyata akkaataa kanaan isaaf dhiyaate ofitti fuudhee simachuun guyyaa 15 (kudha shan) keessatti komii isaa ilaaluun murteessuun qonnaan bulicha, horsiisee bulicha yookiin gamisa horsiisee bulicha beeksisuu qaba.

(b) Koree Bulchiinsa Investimentii Magaalaa ittiwaamamni isaa Naannoof ta'e yeroo jedhame keessatti kan hin murteessine yoo ta'e komii isaa Biirichatti kallattiin iyyachuun akka murta'uuf gochuu qaba. Biirichis guyyaa 10 (kudhan) keessatti komii isaa ilaaluun murteessuun qaama dhimmi ilaaluuf dabarsuu qaba.

(c) Biirichi yeroo jedhame keessatti akkaataa Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 5 fi 7(b)tiin murteesse qaama aangoo qabuuf kan hin ergine yoo ta'e qonnaan bulichi, horsiisee bulichi yookiin gamisa horsiisee bulichi Koree Raawwachiistuu Dhimma Investimentiitti komii isaa dhiyeeffachuu ni danda'a.

8) Bu'uura Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 6 tiin Boordiin murtii kennuun erga beeksiseen booda, Biiroon waliigaltee investimentii isaanii sadarkaa Godinaatti yookiin Bulchiinsa Magaalaa Naannoof ittiwaamamanitti akka mallatteeffamu ni taasisa.



7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 - 5 ሥር የተገለጹት የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት በተባለው ጊዜ ውስጥ የማይወስኑ ከሆነ አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ ወይም ከፊል አርብቶ አደሩ እንደሚከተለው በማመልከት ማስወሰን ይችላል፡-

(ሀ) ተጠሪነቱ ለዞን የሆነ የወረዳና የከተማ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ኮሚቴ በተባለው ጊዜ ውስጥ የማይወስኑ ከሆነ ለዞን የኢንቨስትመንት አስተዳደር ኮሚቴ በቀጥታ በማመልከት በአፋጣኝ እንዲወሰንለት ማድረግ ይችላል፡፡ የዞን ኮሚቴም በዚህ መልኩ የቀረበለትን አቤቱታ በመቀበል ቅሬታውን በ15 (አስራ አምስት) ቀናት ውስጥ በመመርመር ወስኖ ለአርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ ወይም ከፊል አርብቶ አደሩ ማሣወቅ አለበት፡፡

(ለ) ተጠሪነቱ ለክልል የሆነ የከተማ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ኮሚቴ በተባለው ጊዜ ውስጥ የማይወስኑ ከሆነ ቅሬታውን ለቢሮው በቀጥታ በማቅረብ እንዲወሰንለት ማድረግ አለበት፡፡ ቢሮውም በ10 (በአስር) ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በመመርመር ወስኖ ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ አለበት፡፡

(ሐ) ቢሮው በተባለው ጊዜ ውስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 እና 7 (ለ) መሠረት ወስኖ ስልጣን ላለው አካል የማይልክ ከሆነ አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ ወይም ከፊል አርብቶ አደሩ ቅሬታውን ለኢንቨስትመንት ጉዳይ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ቦርዱ ውሳኔ በመስጠት ካሳወቀ በኋላ፣ ቢሮው የኢንቨስትመንት ውላቸው በዞን ወይም ለክልል ተጠሪ በሆነ የከተማ አስተዳደር ደረጃ እንዲፈረም ያደርጋል፡፡



7) Where the Investment Administration Body mentioned under Sub Article 3 - 5 of this Article fail to cause such issue be decided within the time provided, the farmer, pastoralist or semi pastoralist may cause it to be decided by applying in the following manner:

(a) Where the Woreda and City Investment Administration Committee accountable to the Zone fail to get it decided within the time provided, it shall directly apply to the Zonal Investment Administration Committee make it decide for it without delay. The Zonal Committee shall accept the application submitted to it in such manner and by examining and deciding over his complaint within 15 (fifteen) days and shall notify such decision for the farmer, pastoralist or semi pastoralist.

(b) Where the City Investment Administration Committee accountable to the Region fail to get it decided within the time provided, it shall directly apply to the Bureau require to be decided in his favor. The Bureau shall examine and decide on his complaint within 10 (ten) days and send it for the concerned body.

(c) Where the Bureau fails to decide on such issue within the time limited in accordance with Sub Article 5 and 7 (b) of this Article and send it for the concerned body, the farmer, pastoralist or semi pastoralist may lodge his grievance to the Investment Matters Executive Committee.

8) After the Board has decided and notified in accordance with Sub Article 6 of this Article, the Bureau shall cause their investment contractual agreement to be signed at the Zonal level or at the City accountable to the Region levels.

9) Qonnaan Bulaa, Horsiisee Bulaa yookiin Gamisa Horsiisee Bulaan qabeenya qabu carraa investimentii adda baafatee pirojektoota gurmaa'insa pirojektii investimentii naannicha keessatti qoratamee adda bahe irratti gaaffii hojii investmentii dhiyeeffachuu ni danda'a.

10) Qonnaan Bulaa, Horsiisee Bulaa yookiin Gamisa Horsiisee Bulaan lafa qabiyyee dhuunfaa isaa irratti hojii investimentii hojjechuu barbaadu kamiyyuu gurmaa'insa investimentii akkaataa Gurmaa'insa Pirojektoota Investimentii Naannoo Oromiyaa seera rogummaa qabuun tumame eeguuf hin dirqamu.

11) Investerri yookiin Qonnaan Bulaan, Horsiisee Bulaan yookiin Gamisa Horsiisee Bulaan qabeenya horateefi qonnaan bulaan, horsiisee bulaan yookiin gamise horsiisee bulaan qabiyyee lafa tajaajila investimentiif oolu qabu waliin akkaataa seera rogummaa qabuutiin waldaan gurmaa'anii gaaffii hayyama investimentii dhiyeeffachuu ni danda'u.

12) Qonnaan Bulaan, Horsiisee Bulaan yookiin Gamisa Horsiisee Bulaan qabiyyeen lafa isaa hojii investimentii qonnaatiif barbaadame laficha irratti misoomsuuf dandeettii yoo qabaate akkaataa karoora ittifayyadama lafaatiin yookiin pilaanii magaalaatiin dhuunfaan yookiin waldaan gurmaa'ee mirga dursa misoomsuu ni qabaata.

13) Qonnaan Bulaan, Horsiisee Bulaa yookiin Gamisa Horsiisee Bulaa sababa misoomaatiif lafa isaanii irraa kaafaman dhuunfaan yookiin gurmaa'uun hojii investimentii keessa akka galan qaama dhimmi ilaaluun calalamanii dhiyaataniif koree dhimmi ilaaluun deeggarsi addaa ni taasifama.

9) ባለሃብት የሆነ አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር የኢንቨስትመንት አማራጩን በመለየት በክልሉ ውስጥ ተጠንቶ በተለየው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት አደረጃጀት ላይ የኢንቨስትመንት ስራ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

10) በራሱ የመሬት ይዞታ ላይ የኢንቨስትመንት ስራ ለመስራት የሚፈልግ ማንኛውም አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር በኦሮሚያ ክልል የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አደረጃጀት መሠረት አግባብነት ባለው ሕግ የተደነገገውን የኢንቨስትመንት አደረጃጀትን ለመጠበቅ አይገደድም፡፡

11) ኢንቨስተር ወይም ሃብት ያፈራ አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር እና ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚውል መሬት ካለው አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር ጋር አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት በማሕበር በመደራጀት የኢንቨስትመንት ስራ ፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

12) መሬቱ ለግብርና ኢንቨስትመንት የተፈለገ አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር በመሬቱ ለማልማት አቅም ካለው በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ወይም በከተማ ፕላን መሠረት በግሉ ወይም በማሕበር በመደራጀት መሬቱን ቅድሚያ የማልማት መብት ይኖረዋል፡፡

13) በልማት ምክንያት ከመሬታቸው የተነሱ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች በግል ወይም በመደራጀት ወደ ኢንቨስትመንት ሥራ እንዲገቡ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ተለይተው ለቀረቡት ጉዳዩ በሚመለከተው ኮሚቴ ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

9) The wealthy farmer, pastoralist or semi pastoralist may, by identifying the investment opportunity submit his application for investment work on the projects which are studied and identified in the investment projects categorization of the Region.

10) Any farmer, pastoralist or semi pastoralist who wants to perform investment work on his private land possession shall not be obliged to observe the investment categorization as the investment projects categorization of Oromia Region provided under pertinent laws.

11) The investor, farmer, pastoralist or semi pastoralist who acquired assets may be organized in Association as per the pertinent law with the farmer, pastoralist or semi pastoralist who possess land holding to be used for investment and submit application for investment license.

12) Where the farmer, pastoralist or semi pastoralist whose land possession is required for agricultural investment works has the capacity to undertake development on such land, he shall have priority right of developing such land as per the land use plan or in line with the urban plan privately or being organized in association.

13) For the farmers, pastoralists or semi pastoralists expropriated of their land holdings for development reasons that are screened out and reported by the concerned body to engage in to investment works privately or being organized in association, special support shall be given or made by the Committee which the issue concerns.

14) Pirojektiin investimentii Qonnaan Bulaan, Horsiisee Bulaan yookiin Gamisa Horsiisee Bulaan qabiyyee lafa isaa magaalaa keessa jiru irratti dhiyeeffatu pilaanii magaalaatiin kan walsimu ta'uu qaba.

**14. Hojii Investimentiitti Ce'uuf Ulaagaalee Guutamuu Qaban**

1) Qonnaan Bulaan, Horsiisee Bulaan yookiin Gamisa Horsiisee Bulaan gara investimentiitti ce'uuf barbaadu ulaagaalee armaan gadii guutuu qaba:

(a) Iyyannoo gaaffii pirojektii investimentii;

(b) Yeroo gaaffii investimentii dhiyeeffatutti Ganda hojii qonnaa keessatti gaggeessa ture yookiin jiru irraa waggaa 10 (kudhan) fi isaa ol hojii qonnaan yookiin horsiisee bulaan yookiin gamisa horsiisee bulaan jiraachuu isaa kan ibsu waraqaa deeggarsaa qaama bulchiinsaa dhimmi ilaallatu irraa dhiyeessuu;

(c) Waraqaa ragaa mirkaneessa abbaa qabiyyummaa lafaa qaama aangoo qabuun kennameef;

(d) Qonnaan Bulaa waraqaa ragaa qabiyyee lafaa osoo hin qabaatiin sababa babal'ina magaalaatiin daangaa bulchiinsa magaalaa jala gale yoo ta'e, nagahee gibiraa itti fayyadama qabiyyee lafaa waggaa 5f (shaniif) ittiin kaffale;

(e) Waraqaa eenyummaa haaromfame jiraataa bulchiinsa ganda baadiyyaa yookiin magaalaa naannichaa ta'uu isaa ibsu;

(f) Horsisee Bulaan qabeenya horatee investimantiitti ce'uuf gaaffii dhiyeeffatu, hojii misooma beeyladaa irratti bobba'uu isaa waraqaa deeggarsa qaama dhimmi ilaallatuun kenname;

(g) Pirojektii investmentii dhuunfaadhaan yookiin maatiidhaan waldaan gurmaa'uun yookiin namoota maatiin ala jiraniin waldaan gurmaa'uun hojii investimentiitti bobba'uuf gaaffii dhiyeessuuf kaappitaala waliigalaa qarshii 5,000,000.00 (miliyoona shan)fi isaa ol kan horate ta'uu ragaa agarsiisu;



14) አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ ወይም ከፊል አርብቶ አደሩ በከተማ ውስጥ ባለው መሬቱ ላይ የሚቀርበው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ከከተማው ፕላን ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡

**14. ወደ ኢንቨስትመንት ስራ ለመሸጋገር መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች**

1) ወደ ኢንቨስትመንት ለመሸጋገር የሚፈልግ አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር ከዚህ በታች ያሉትን መስፈርቶችን አሟልቶ መቅረብ አለበት፤

(ሀ) የኢንቨስትንት ፕሮጀክት ጥያቄ ማመልከቻ፤

(ለ) ይህንን የኢንቨስትመንት ጥያቄ ሲያቀርብ የግብርና ስራ ስሰራበት ከነበረ ቀበሌ ወይም ይኖርበት ከነበረበት ቀበሌ 10 (አስር) ዓመትና ከዚያ በላይ በግብርና ስራ ወይም በአርብቶ አደርነት ወይም በከፍል አርብቶ አደርነት መኖሩን የሚያሳይ የድጋፍ ደብዳቤ ከምመለከተው መስተዳድር አካል ማቅረብ፤

(ሐ) ስልጣን ካለው አካል የተሰጠው የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ፤

(መ) የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሳይኖረው አርሶ አደር በከተማ መስፋፋት ምክንያት የመሬት ይዞታው ከተማ መስተዳድር ስር ከገባ ለ5 (አምስት) ዓመት የመጠቀሚያ ግብር የገበረበት ደረሰኝ፤

(ሠ) የክልሉ የገጠር ወይም የከተማ መስተዳድር ቀበሌ ነዋሪ መሆኑን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ፤

(ረ) ወደ ኢንቨስትመንት ስራ ለመሸገጋገር ጥያቄ የምያቀርብ አርብቶ አደር በከብት እርባታ ስራ ላይ መሰማራቱን ከሚመለከተው አካል የድጋፍ ደብዳቤ፤

(ሰ) በግል ወይም በቤተሰብ በማህበር በመደራጀት ወይም ከቤተሰብ ውጭ ካሉት ሰዎች ጋር በማህበር በመደራጀት ወደ ኢንቨስትምንት ስራ ለመግባት ጥያቄ ለማቅረብ 5,000,000 (አምስት ሚሊዮን ብር) እና ከዚያ በላይ ካፒታል ማፍራቱን የሚያሳይ ማስረጃ ማሳየት፤



14) Application for investment project submitted by the farmer, pastoralist or semi pastoralist on his land possession found in the City shall be in compliance with the urban plan.

**14. Requirements to be Satisfied to Promote to Investment Activities**

1) The Farmer, Pastoralist or Semi-pastoralist wishing to promote to investment shall meet the following requirements:

(a) Investment project request application;

(b) Submit a letter of support or recommendation given from the relevant administrative body stating that he has been engaged in agriculture or pastoral or semi-pastoral activities for 10 years or more from the kebele where has been conducting agricultural activities at the time of submitting the investment application;

(c) A certificate of title deed/land holder's certificate issued by the competent authority;

(d) If the farmer included under the urban administration boundary due to urban expansion without having a title deed land holding certificate, a receipt for payment of land use tax for five years;

(e) A renewed identity card stating that he is a resident of a rural or urban kebele village administration of the Region;

(f) Letter of support issued by the relevant authority indicating that he is engaged in livestock development activities for pastoralist who acquired property and submit request to promote to investment;

(g) Proof of having raised a total capital of 5,000,000 (five million) birr or more to apply for engaging on investment projects individually or being organized by families or by persons outside the family;

(h) Yeroo gaaffichi dhiyaatetti kaappitaala waliigalaa hojichaaf galmeessise keessaa %20 (digdama) qabaachuu isaa kan agarsiisu ragaa baankii irra kenname;

(i) Waldaan gurmaa'uun gaaffii investimentii kan dhiyaatu yoo ta'e, barreeffama hundeeffamaa qaama aangoo qabuun mirkanaa'e dhiyeessuu;

(j) Karoora bu'aa qabeessummaa hojii pirojektichaa dhiyeessuu.

2) Ulaagaan Keewwata kana Keewwata Xiqqaa 1 (b) jalatti tumame nama maatii Qonnaan Bulaa, Horsiisee Bulaa yookiin Gamisa Horsiisee Bulaa ta'ee mirga ittifayyadama lafaa seeraan argate irratti raawwatiinsa hin qabaatu.

**15. Qonnaan Bulaa, Horsiisee Bulaa yookiin Gamisa Horsiisee Bulaaf Hayyama Investimentii Kennuuf Ulaagaa Barbaachisu**

1) Qonnaan Bulaan, Horsiisee Bulaan yookiin Gamisa Horsiisee Bulaan lafa qabiyyee dhuunfaa isaa irratti hojii investimentii ofiin gaggeessuuf hayyama investimentii gaafatu ulaagaalee armaan gadii guutuu qaba:

(a) Iyyannoo gaaffii hayyama investimentii guca Biiroodhaan qophaa'u irratti guutuun dhiyeessuu;

(b) Kooppii waraqaa eenyummeessaa kan haaromfame suuraa waliin;

(c) Qorannoo karoora bu'a qabeessummaa hojii pirojektichaa;

(d) Waraqaa ragaa abbaa qabiyyummaa lafaa qaama aangoo qabuun kennameef;

(e) Kaappitaala pirojektichaaf barbaachisu keessaa % 20 (digdama) fi sanaa ol qusachuu isaa ragaa agarsiisu Baankii irraa kennameef;

(f) Kaffaltii tajaajilaa Qajeelfama bahuun murtaa'u kaffaluu isaa nagahee agarsiisu;

(g) Pirojektichi qorannoo sakatta'iinsa dhiibbaa naannoo kan barbaachisu yoo ta'e qaama aangoo qabu irraa ragaa kenname;

(h) Iyyanni dhiyaatu bakka bu'aan yoo ta'e, ragaa bakka bu'uummaa qaama aangoo qabuun kenname.



(ሸ) ጥያቄው ሲቀርብ አጠቃላይ ለስራው ካስመዘገበው ካፒታል ውስጥ %20 (ሀያ ፐርሰንት) ያለው መሆኑን የሚያሳይ ከባንክ የተሰጠ ማስረጃ፤

(ቀ) በማህበር ተደራጅተው ኢንቨስትምንት የሚጠይቅ ከሆነ ስልጣን ባለው አካል የጸደቀ የመመስረቻ ጽሁፍ ማቅረብ፤

(ተ) የፕሮጀክቱ ስራ የአዋጭነት እቀድ ማቅረብ፡፡

2) ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) ስር የተደነገገው የአርሶ አደር፣ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር ቤተሰብ ሆኖ በመሬት የመጠቀም መብትን በህግ ባገኘ ሰው ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**15. ለአርሶ አደር፣ አርብቶ አደር ወይም ለከፊል አርብቶ አደር የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ማሟላት ያለባቸው መሳፈርቶች**

1) በራሱ የግል ይዞታ መሬት ላይ የኢንቨስትመንት ስራዎችን በራሱ ለመስራት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚጠይቅ አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር ወይም ከፍል አርብቶ አደር የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፤

(ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት ቢሮው በሚያዘጋጀው ቅጽ ላይ ማመልከቻ ሞልቶ ማቅረብ፤

(ለ) የታደሰ መታወቂያ ካርድ ኮፒ ከፎቶግራፍ ጋር፤

(ሐ) የፕሮጀክቱ ስራ ውጤታማነት እቅድ ጥናት፤

(መ) ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የመሬት አጠቃቀም የምስክር ወረቀት፤

(ሠ) ለፕሮጀክቱ ከሚያስፈልገው ካፒታል %20 (ሃያ ፐርሰንት) ኢና ከዚያ በላይ መቆጠቡን የሚያሳይ ከባንክ የተሰጠ ማስረጃ፤

(ረ) በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን የአገልግሎት ክፍያ መክፈሉን የሚያሳይ ደረሰኝ፤

(ሰ) ፕሮጀክቱ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት የሚያስፈልገው ከሆነ ስልጣን ባለው አካል የተሰጠ ማስረጃ፤

(ሸ) ማመልከቻው በተወካይ የሚቀርብ ከሆነ ስልጣን ባለው አካል የተሰጠ የውክልና ምስክር ወረቀት፡፡



(h) Bank evidence showing that he has 20% (twenty percent) of the total capital registered for the business at the time of request;

(i) If the request for investment is submitted by being organized in Association, submission of a memorandum of association approved by the competent authority;

(j) Presenting the project operational effectiveness plan.

2) The requirement under sub-article 1(b) of this Article shall not apply to a person who is a member of a family of a Farmer, Pastoralist or Semi-pastoralist who has legally acquired land use rights.

**15. Requirements for Issuing Investment Licenses to Farmers, Pastoralists or Semi-Pastoralists**

1) The farmer, pastoralist or semi-pastoralist applying for an investment license to conduct investment activities on his own land holding shall meet the following requirements:

(a) Fill out the application for investment license on the form prepared by the Bureau;

(b) Renewed copy of identity card with photograph;

(c) Study of the project's operational effectiveness plan;

(d) land holder certificate issued by a competent authority;

(e) Evidence from the Bank showing that he has saved 20% (twenty percent) and more of the capital required for the project;

(f) A receipt showing payment of the service charges to be determined by a directive to be issued;

(g) Evidence given from the competent authority if the project requires an environmental impact assessment study;

(h) If the application is made by a representative, evidence of representation issued by the competent authority.

2) Qaamni hayyama investimentii kennu Qonnaan Bulaa, Horsiisee Bulaan yookiin Gamisa Horsiisee Bulaan pirojektii investimentii lafa qabiyyee dhuunfaa yookiin mootummaa isaa irratti hojjechuuf karoorfame gurmaa'insa investimentii Dambii Gurmaa'insa Pirojektoota Investimentii Naannichaa eeguuf hin dirqamu.

### 16. Deeggarsa Addaa

1) Deeggarsi akkaataa seerota birootiin taasifamuuf akkuma eegametti ta'ee, Qonnaan Bulaa, Horsisee Bulaa yookiin Gamisa Horsiisee Bulaa gara investimentiitti ce'aniif deeggarsi addaa armaan gadii taasifamuufii ni danda'a:

(a) Hubannoo carraa investimentii, ulaagaalee guutamuu qabanii, adeemsa gaaffiin pirojektii investimentii itti dhiyaatuufi haala inshuraansii itti argatan;

(b) Deeggarsa qophii karoora bu'a qabeessummaa pirojektii investimentii irratti ogeessota Aanaa yookiin Magaalaa yookiin manneen hojii dhimmi ilaallatuun argachuu;

(c) Lafa investimentii magaalaa keessaa irratti gaaffii dhiyaatuuf, gosa pirojektii investimentii hundaaf ramaddiin argachuu;

(d) Meeshaalee adda addaa hojii investimentiif barbaachisu qaama dhimmi ilaalu irraa argachuu;

(e) Jajjabeessituu gibira irraa bilisa ta'uufi meeshaalee adda addaa pirojektichaaf isa barbaachisuufi seeraan hayyamame ashuuraan ala biyya alaa irraa akka galfatu deeggarsa argachuu;

(f) Pirojektii investimentii murtii Boordii argachuun gaggeessu kamiyyuu bara turtii waliigaltee pirojektii investimentii keessatti kaffaltii liizii yookiin kiraa lafaa irraa bilisa ta'uu;



2) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰጪው አካል አርሶ አደር፤ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር በግል ይዞታ መሬቱ ላይ ወይም በመንግስት መሬት ላይ ለማካሄድ የታቀደውን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት በኦሮሚያ ክልል የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አደረጃጀት ደንብ ለመጠበቅ አይገደድም፡፡

### 16. ልዩ ድጋፍ

1) ወደ ኢንቨስትምንት ለተሸጋገሩ አርሶ አደር፤ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር በሌሎች ህጎች የሚደረግለት ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው ልዩ ድጋፍ ሊደረግለት ይችላል፤

(ሀ) የኢንቨስትመንት እድሎች፣ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፤ የኢንቨስትመንት ጥየቄ የሚቀርብበት ሂደትን እና መድን የምያገኙበት ሁኔታን በተመለከተ ግንዛቤ ማግኘት፤

(ለ) ውጤታማ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት እቅድ አዘጋጃጀት ላይ ከወረዳ ወይም ከተማ ወይም ጉዳዩ ከሚመለከተው መስሪያ ቤት የባለሙያዎች ድጋፍ ማግኛት፤

(ሐ) በከተማ ውስጥ ለሚቀርብ የኢንቨስትመንት ጥያቄ መሬት ለሁሉም አይነት የኢንቨስትመንት ፕሮአጀክት በምደባ የሚሰጠው ይሆናል፤

(መ) ለኢንቨስትመንት ስራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ቁሳቁሶች ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ማግኘት፤

(ሠ) ከግብር ነጻ ማበረታቻ እና ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉት የተለያዩ በህግ የተፈቀዱ ቁሳቁሶችን ከአሹራ በነጻ ከውጪ ሀገር እንዲያስገባ ድጋፍ ማግናት፤

(ረ) በቦርድ ውሳኔ ባገኙት የትኛውም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ላይ ስራ የሚያካሄድ ከሆነ ከመሬት ኪራይ ወይም ከሊዝ ነጻ መሆን፤



2) The investment licensing body shall not be obliged to comply with the investment organization of the Region for investment projects a Farmer, Pastoralist or Semi-Pastoralist planned to carry out on his private land holding or government land.

### 16. Special Support

1) Without prejudice to the support provided in accordance with other laws, the following special support may be provided to the Farmer, Pastoralist or Semi-Pastoralist who are promoted to investment:

(a) Understanding raising of investment opportunities, requirements to be met, the process for applying for investment projects and the manner of obtaining insurance;

(b) Receive support for the preparation of an investment project effectiveness plan from experts of Woreda or City or relevant government institutions;

(c) Obtaining land by allocation for all types of investment project requests in the city;

(d) Obtaining various equipment required for investment activities from the relevant authority;

(e) Obtaining tax exemption and assistance to import tax free various materials required for the project and permitted by law;

